**ፀሐይ ባንክ ከቅዱስ ጊዮርጊስ የእግር ኳስ ክለብ ጋር ለመሥራት የአጋርነት ስምምነት ተፈራረመ**

ስምምነቱ የተፈፀመው ፀሐይ ባንክ የአሸናፊዎች የቁጠባ ሒሳብ ማስጀመሪያ መርሐግብር መስከረም 05 ቀን 2016 ዓ.ም ባካሔደበት ወቅት ነው።

የአሸናፊዎች የቁጠባ ሒሳብ / Champions Saving Account ለኢትዮጵያ እግር ኳስ ክለቦች እና ደጋፊዎቻቸው የተዘጋጀ የቁጠባ ሒሳብ ሲሆን በደጋፊዎች የተቀማጭ ገንዘብ ላይ በመስራት ለክለቦች አስፈላጊውን የፋይናንስ ድጋፍ የሚያስገኝ መሆኑ ተገልጿል፡፡

ፀሐይ ባንክ የአሸናፊዎች የቁጠባ ሒሳብን ለማስጀመር በመጀመሪያ ምዕራፍ ከቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ክለብ ጋር ስምምነት አድርጓል።

የመግባቢያ ስምምነቱን የፀሐይ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ያሬድ መስፍን እና የቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ክለብ ፕሬዝዳንት አቶ አብነት ገብረመስቀል ተፈራርመዋል፡፡

በስምምነቱ መሰረት የእግር ኳስ ክለቡ ደጋፊዎች በፀሐይ ባንክ የአሸናፊዎች የቁጠባ ሒሳብ በመክፈት ሲቆጥቡ ከባንኩ ከሚያገኙት የተቀማጭ ወለድ አንድ በመቶ ለክለቡ ገቢ ይደረጋል።

የክለቡ ደጋፊዎች የአሸናፊዎች የቁጠባ ሒሳብ ሲከፍቱ ከተከፈተው ሒሳብ ተቀናሽ የሚደረግ የተወሰነ ብር ወዲያውኑ ለክለቡ የሚተላለፍ ይሆናል፡፡

በተጨማሪም በየዓመቱ በ10 በመቶ የሚያድግ የአምስት ሚሊዮን ብር የስፖንሰርሺፕ ገቢ ከፀሐይ ባንክ ለክለቡ ገቢ እንደሚደረግ ተገልጿል፡፡

ለቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ክለብ የልምምድ ቦታ ግንባታ የሚውል እሰከ 40 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ የረጅም ጊዜ ብድር የተመቻቸ መሆኑንም የፀሐይ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ያሬድ መስፍን ተናግረዋል፡፡

ፀሐይ ባንክ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ኢንዱስትሪን ለማገዝ እና ውጤታማነቱን ለማረጋገጥ የሻምፒዮን/የአሸናፊዎች የቁጠባ ሒሳብ ይዞ መምጣቱንም ዋና ሥራ አስፈጻሚው ገልጸዋል፡፡

በስምምነቱ መፈፀም ደስታቸውን የገለፁት የቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ክለብ ፕሬዝዳንት አቶ አብነት ገብረመስቀል፤ ስምምነቱ ለአምስት ዓመታት የሚቆይ አጋርነት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ስምምነቱ ለሁለቱም ተቋማት በርካታ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ያነሱት አቶ አብነት፤ ፀሐይ ባንክ በክለቡ የማህበራዊ ገፆች፣ ጋዜጣ፣ ሳምንታዊ የሬዲዮ መሰናዶ እንዲሁም በተለያዩ የግንኙነት መንገዶች አገልገሎቶቹን የማስተወዋወቅ ዕድል እንደሚኖረውም አረጋግጠዋል።

ስምምነቱ ለጊዮርጊስ ደጋፊዎች የሚኖረው ተጫማሪ ፋይዳ፡-

- የክለቡ ደጋፊዎች የአባልነት ክፍያቸውን በፀሐይ ባንክ በኩል እንዲከፍሉ ይደረጋል፣

- ለክለቡ ተጫዋቾችም ሆነ ሰራተኞች ወርሃዊ ደምወዝ በፀሐይ ባንክ በኩል ይከፈላል፣

- በባንኩ የሚያንቀሳቅሱት ገንዘብ ባደገ ቁጥር ባንኩ ድጋፉ እያደገ ይሄዳል ።

- የስታዲየም መግቢያ ቲኬቶች እና የክለቡ ቲሸርተና አልባሳት በፀሐይ ባንክ ቅርንጫፎች እንዲሸጥ ይደረጋል፣

- የክለቡ የተለያዩ የገቢ ማስገኛና ክፍያዎች ሁሉ በፀሐይ ባንክ በኩል የሚፈፀም ሲሆን ይህም ክለቡንም ባንኩም የበለጠ ተጠቃሚ ያደርጋል።

**ፀሐይ ባንክ**

**ለሁሉ!**